**ማ ው ጫ**

**ርዕስ**


**መግቢያ** ............................ ............................ 1

**ክፍል አንድ**

1. **የዳያስፖራ ተሳትፎ ነባራዊ ሁኔታዎች ቅኝት** ...................... 2
   1.1. የዳያስፖራ ተሳትፎ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ...................... 2
   1.2. የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ተሳትፎ ቅኝት .................... 3
2. **የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ፖሊሲ መነሻና አስፈላጊነት** .................... 4
3. **የዳያስፖራ ተሳትፎ ፖሊሲ ትርጉምና ዓላማ** .................... 5
   3.1. ትርጉም .................... 5
   3.2. የዳያስፖራ ፖሊሲው አጠቃላይ ዓላማ ............ .......... 5

**ክፍል ሁለት**

4. **የፖሊሲው መሰረታዊ መርሆዎች** ..................... 6
   4.1. ሴክተር አቀፋዊነት (A sector Wide Approach) ...................... 6
   4.2. ውጤታማነት (Effectiveness) ..................... 6
   4.3. የሃብት አጠቃቀም (Resources Utilization) ...................... 6
   4.4. ተደጋጋፊነት (Complementarity) ..................... 6
   4.5. አሳታፊነት (Participatory) ...................... 6
   4.6. ግልጽነት (Transparency) ..................... 6
   4.7. አጋርነት (Partnership) ...................... 6
5. **የፖሊሲው ዋና ዋና ግቦች** ..................... 7
   5.1. በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንን መብትና ጥቅም ማስጠበቅ .................... 7
   5.2. የኢንቨስትመንት፣ የንግድና ቱሪዝም ተሳትፎን ማጐልበት ................. 7
   5.3. የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ ...................... 9
   5.4. የውጭ ምንዛሪ ማስገቢያ መንገዶችንና ተሳትፎን ማሳደግ ................... 9
   5.5. ባህላዊ ዕሴቶችን ማዳበርና ገፅታ ግንባታን ማትጋት ..................... 10
   5.6. በዴሞክራሲያዊ ሂደት የሚኖረውን ተሳትፎ ማሳደግ ...................... 10
   5.7. የግብረ ሰናይና የልማት ማህበራትን ማትጋት ...................... 11
   5.8. የኢትዮጵያን ገፅታ በሚነካቡ ጉዳዮች ላይ ማሳተፍ ..................... 11

**ክፍል ሶስት**

6. **የፖሊሲው ስትራቴጂዎች** ..................... 12
   6.1. አስተማማኝ የመረጃ አያያዝና ሥርጭት ሥርዓት መዘርጋት ........................ 12
   6.2. ለዳያስፖራው ተሳትፎ ዕውቅና መስጠ ..................... 13
   6.3. የተደራጀ ተሳትፎን ማትጋት ...................... 13
   6.4. የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ መስጠት ...................... 14
   6.5. የዳያስፖራ አባላትን መደገፍ ................. ..... 14
7. **የፖሊሲው አስፈፃሚ አካላት** ................... 15

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌዴራራላዊ ዴሞክራራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የዳያስፖራውን ተሳትፎ የማሳደግና በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንን መብትና ጥቅማቸውን የማስከበር ሥልጣንና ኃላፊነት ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስጠቱ ይታወቃል፡፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱም በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላትን ተሳትፎ ለማጎልበትና መብትና ጥቅማቸውን ለማስከበር የበኩሉን ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በዚህም ጅምር እንቅስቃሴ በርካታ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት መዋዕለ ንዋያቸውን ሀገር ውስጥ በማፍሰስ፣ ዕውቀትና ቴክኖሎጂን በማሸጋገር፣ የውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገር ውስጥ በመላክ፣ ንግድና ቱሪዝምን በማስፋፋትና፣ የሀገራችንን ገጽታ በመገንባት ረገድ ተጨባጭ ውጤቶችን በማስመዝገብ ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህንም በጎ ጅምሮች በማጎልበት ዳያስፖራውን በሀገሩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት በማሳተፍ ራሱንና ሀገሩን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል ፖሊሲ መቅረጽ ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ ሆኗል፡፡

በዚህ መሰረት በዳያስፖራው ጉዳዮች ዙሪያ የቆዩ መመሪያዎችንና አፈፃፀሞችን በዝርዝር በማጥናት፣ የተለያዩ ጽሁፎችንና የተሞክሮ ልውውጥ መድረኮችን እንዲሁም የሌሎች አገሮች ጠቃሚ ልምዶችን በግብአትነት በመጠቀምና ከዳያስፖራው የተሰጡ አስተያየቶችን በማካተት ይህ የፖሊሲ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

ይህ የዳያስፖራ ፖሊሲ በሶስት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን በመጀመሪያው ክፍል የዓለም አቀፍና የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ነባራዊ ሁኔታዎች ዳሰሳ፣ ትርጉም፣ ዓላማ እንዲሁም የፖሊሲውን አስፈላጊነት በሚመለከቱ ነጥቦች ላይ የሚያተኩር ሲሆን፣ በሁለተኛው ክፍል የፖሊሲው መሠረታዊ መርሆዎችና ዋና ዋና ግቦች ተካተዋል፣ ሦስተኛው ክፍል ደግሞ የፖሊሲው ስትራቴጂዎችና አስፈፃሚ አካላትን የሚያመለክት ነው፡፡

## ክፍል አንድ

## 1. የዳያስፖራ ተሳትፎ ነባራዊ ሁኔታዎች ቅኝት

### 1.1 የዳያስፖራ ተሳትፎ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች

የሰው ልጅ በተለያዩ ምክንያቶች ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር ከጀመረ ዘመናትን አስቆጥሯል፡፡ የታሪክ ጸሀፊዎች ከምስራቅ አፍሪካ ተነስቶ ወደ ሌላው የዓለም ክፍል የተደረገው የሰዎች እንቅስቃሴ የመጀመሪያው ፍልሰት ነው ይሉታል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ዘመናት የተለያዩ ገጽታ ያላቸው የሰዎች ፍልሰት ተከስቷል። ይሁን እንጂ በከፍተኛ ቁጥር ብዛት ያለው የሰዎች ዝውውር በአንጻራዊነት የቅርብ ጊዜ ታሪክ ያለው ነው፡፡

ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ ግሎባላይዜሽን ከፈጠረው ሁኔታ ጋር  በተያያዘ የካፒታል ፣ የምርቶች፣ የመረጃና ሌሎች ጉዳዮች ዝውውር እያደገ መምጣቱን ተከትሎ የሰው ልጆች ፍልሰትም በከፍተኛ ደረጃ ሊያድግ ችሏል፡፡ በተለይም ዘመኑ ዕውን ያደረጋቸው ፈጣን፣ ቀልጣፋና አስተማማኝ የመገናኛና የትራንስፖርት አውታሮች ለሰዎች ዝውውር መጨመር የራሳቸውን አስተዋፅዖ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በዓለም ከ200 ሚሊዮን በላይ ሰዎች ማለትም ከዓለማችን ጠቅላላ ህዝብ ሶስት ፐርሰንት የሚሆነው  ከትውልድ አገሩ ውጭ የሚኖር ሲሆን፣ ይህ ቁጥር በየዓመቱ የ2.9 ፐርሰንት ዕድገት እንደሚኖረዉ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ምንም እንኳን ፍልሰት በጦርነት እና መሰል ጉዳዮች አስገዳጅነት የሚሰደዱትን የሚያጠቃልል ቢሆንም አሁን በአብዛኛው እየጨመረ በመምጣት ላይ ያለው  ፍልሰት በበለጸጉት አገሮች ብዙ ነው ተብሎ ከሚታሰቡ ምቹ ሁኔታዎችና ዕድሎች በሌላ በኩል ደግሞ በታዳጊ አገሮች ካለው የልማት እንቅስቃሴ ደካማ መሆን እና ብዙ የስራ ዕድል ካለመኖር ጋር በተያያዙ ምክንያቶች የሚከሰት መሆኑ ይስተዋላል።

ፍልሰት ስለሚያስገኛቸው ጥቅምም ሆነ ስለሚያስከትለው ጉዳት በመነሻ እና መዳረሻ አገሮች ዘንድ በተለያየ መልክ ይታያል፡፡ በአንድ በኩል ፍልሰት የመነሻ አገርን የተማረ ወይም አምራች የሰው ኃይልን የሚያሳጣ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ጎጂ ነው የሚል ያለ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በውጭ አገር በስደት የሚገኙ ዜጎች ለቤተሰቦቻቸው ገንዘብ በመላክ ፣ በእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በኢንቨስትመንት ወዘተ መስኮች ለትውልድ ሃገራቸው ልማትና ዕድገት ከሚያበረክቷቸው በጎ አስተዋፅዎች አንጻር ጠቃሚ ነው በማለት የሚከራከሩ አሉ፡፡ ይሁን እንጂ ዜጎች በስደት ላይ ሆነው ለአገራቸው ሊያበረክቱ የሚችሉት አስተዋፅኦ ከአገር ሳይወጡ ማበርከት ከሚችሉት ጋር ሲነፃፀር ውስን ነው የሚለው ሃሳብ ብዙዎችን የሚያስማማ ሆኖ ይታያል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ መዳረሻ  አገሮችም ስደት በአንድ በኩል የዜጎቻቸውን የስራ ዕድል ያጣብባል ብለው ሲኮንኑ፣ በተቃራኒው ደግሞ በሰው ሃይል እጥረት ምክንያት የሚያጋጥሟቸውን የስራ ክፍተቶች በመሙላት ረገድ ጠቃሚነቱን ይገልፃሉ፡፡

የሆነው ሆኖ መነሻና መዳረሻ ሃገሮች ፍልሰትን ማቆም የማይቻል መሆኑን በመገንዘብ የፍልሰት ጎጂ ጎኖችን በመቀነስ በጋራ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ መስራት የተሻለ አማራጭ መሆኑን መግባባት ላይ የተደረሰበት ጉዳይ ሆኗል፡፡

በመሆኑም ፍልሰትን በትክክለኛ የፖሊሲ አቅጣጫ መምራት ከተቻለ በመነሻ አገሮች ተጨማሪ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የዕውቀት ሽግግር በማስገኘትና ድህነትን በመቀነስ እንዲሁም በመዳረሻ አገሮች ደግሞ የሚኖሩ የሰው ሀይል እጥረቶችን በመሙላት የተሻለ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት የራሱ ሚና ያለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

በዚህም ምክንያት በአሁኑ ጊዜ የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳይ በሁለትዮሽ ግንኙነት፣ በአካባቢያዊና በአለም አቀፍ የትብብር መድረኮች ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ሆኗል፡፡ ለዚህም በርካታ አገሮች ዳያስፖራዎቻቸው ባሉበት ሆነው ወይም ተመልሰው በዕውቀት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በንግድ፣ በቱሪዝም፣ በኢንቨስትመንት ፕሮሞሽንና ተሳትፎ፣ የውጭ ምንዛሪ በማሳደግ፣ በገፅታ ግንባታ፣ ለአገራቸው የመልካም ግንኙነት ድልድይ በመሆንና በበጎ አድራጎት ተግባራት በሰፊው የሚሳተፉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚያስችሉ መዋቅሮችን በመዘርጋትና ፖሊሲ በመንደፍ ላይ የሚገኙ ሲሆን ቀደም ብለው ይህን ተግባራዊ ያደረጉ አንዳንድ አገሮች በዚህ ረገድ ከፍተኛ ውጤቶችን አስመዝግበዋል።

## 1.2. የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ተሳትፎ ቅኝት

ቀደም ሲል ኢትዮጵያ በታሪኳ የፍልሰት መነሻ ሳትሆን መዳረሻ እንደነበረች ከተለያዩ ሀገራትም ፈልሰው የመጡ የሌላ ሀገር ዜጎችን ማለትም አይሁዶች፣ አርመኖች፣ አረቦች፣ ግሪኮች፣ ቱርኮች ወዘተ ተቀብላ በማስተናገድ ትታወቅ የነበረ ሲሆን ዜጎችዋ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና፣ በማህበራዊ ምክንያቶች የትውልድ አካባቢያቸውን ለቀው ወደ ተለያዩ ሀገራት ፈልሰው መኖር ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በአፄ ኃይለስላሴ ሥርዓት ከዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያዊያን ወደ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ሀገሮች በመሄድና በመማር ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ከሞላ ጎደል ሁሉም ወደ አገራቸው ተመልሰው ሲያገለግሉ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

የንጉሱ ስርዓት በአምባገነናዊው ወታደራዊ ደርግ ሲተካ በወቅቱ በውጭ በትምህርት ላይ የነበሩ አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያዊያን በያሉበት ሲቀሩ ጥቂት ዜጎች ወደ ሀገር ቤት ተመልሰዋል፡፡ ይሁን እንጂ በሥርዓቱ አምባገነናዊ ባህርይ ምክንያት አገር ውስጥ የነበረው የተማረው የሰው ሃይልም ሆነ በአጎራባች ሀገሮች ድንበር አካባቢ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን አርሶ አደሮች ተስፋ በመቁረጥና አማራጭ በማጣት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ አገራቸውን ጥለው ለመሰደድ ተገድደዋል፡፡ በመሆኑም በወቅቱ ወደ ሌሎች ቦታዎች የሚሄዱት እንዳሉ ሆኖ ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ ውስጥ ዜጎቻቸው በከፍተኛ ደረጃ በሰሜን አሜሪካ ጥገኝነት ከሚጠይቁ አስር አገራት አንዷ እንድትሆን አድርጓታል፡፡

ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላም ቢሆን ዜጎች ከፍተኛ የትምህርት ዕድል ለማግኘት፣ በውጭ አገሮች የሚሰጡ የተለያዩ የመኖሪያ ፈቃዶች ተጠቃሚ ለመሆንና የተሻለ ክፍያ የሚያስገኙ የስራ ዕድሎችን ለመፈለግ ወደ ውጭ ሀገር ይሄዳሉ፡፡

በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ጠቅላላ ብዛታቸው በግምት ከ 2 ሚሊዮን የማያንሱ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት በሰሜን አሜሪካ፣ አውሮፓ፣ መካከለኛው ምስራቅ፣ አውስትራሊያና አፍሪካ አገሮች ውስጥ እንደሚገኙ የሚገመት ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በሰሜን አሜሪካና አውሮፓ የሚገኙት በተነፃፃሪነት የተሻለ ገቢና የትምህርት ዝግጅት እንዳላቸው ይታመናል፡፡

በሰሜን አሜሪካና አውሮፓ የሚኖሩ የዳያስፖራ አባላት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሀገር ውስጥ በተለያዩ መስኮች መዋዕለ ንዋያቸውን በማፍሰስ፣ ዕውቀትና ቴክኖሎጂን በማሸጋገር፤ ወደ ሀገራቸው የውጭ ምንዛሪ በመላክና ወዘተ…

ቤተሰቦቻቸውንና አገራቸውን መርዳት ከመጀመራቸውም በላይ የሀገሪቷን ገፅታ በመገንባትና ለሀገራቸው ጥብቅና በመቆም ረገድ አስተዋፅዖ ማበርከት ጀምረዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በመካከለኛው ምስራቅ የተፈጠረውን የጉልበት ስራ ዕድል ለመጠቀም ወደ አካባቢው የተጓዙ ብዛት ያላቸው ወገኖች የሙያ ሥልጠና ያልወሰዱ እንዲሁም ሙያተኞች ለአገርና ለመንግስት ጥሪ ፈጥኖ በመድረስና በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች በመሰማራትና  ለቤተሰቦቻቸው ገንዘብ ወደ ሀገር በመላክ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ የሚደረገው መደበኛ ያልሆነ የሰዎች ዝውውርና የሥራ ስምሪት እያደገ መምጣቱ በአንድ በኩል የዜጎችን ሙብት በማስጠበቅ ረገድ ውስብስብ ሁኔታዎችን የፈጠረ ቢሆንም፤ በሌላ በኩል ደግሞ ያለውን ውስብስብ ችግር በሂደት እየፈቱ ካለው ሰፊ ዳያስፖራ የተሻለ ሃገራዊ ጠቀሜታ ማግኘት የሚቻልበት ዕድል ስለመኖሩ አመላካች እየሆነ መጥቷል፡፡

ከቅርብ አመታት ወዲህ ከአፍሪካ በተማሩም ሆነ ባልተማሩ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ በመዳረሻ ሀገርነት እየተመረጠች ያለችው ደቡብ አፍሪካ ስትሆን፤ ከባለሙያዎች ፍልሰት አንፃር ደግሞ ቦትስዋናና ኢኳቶሪያል ጊኒ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በመሆኑም በእነዚህ አካባቢዎች ከሚኖሩ ዳያስፖራዎች ጋር የቅርብ ትስስርና የተመቻቸ ሁኔታ በመፍጠር እነርሱንና ሀገሪቷን ተጠቃሚ የማድረግ ሥራ ዕድል ይኖራል ተብሎ ይታመናል፡፡

ከእነዚህ በተጨማሪ በመላው ዓለም የሚገኙ አዲስ ትውልድ ዳያስፖራዎችና በጉዲፈቻነት ወደ ምዕራቡ ዓለም እየፈለሱ ያሉ ህፃናት ቁጥርም በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ እነዚህን አዲስ ትውልድ ወጣቶችና የጉዲፈቻ ልጆች ከትውልድ አገራቸው ባህል፣ ቋንቋ እና ሌሎች ማህበራዊ እሴቶች ጋር ከወዲሁ በማስተሳሰር ለወደፊቱ የሃገሪቱ እሴት እንዲሆኑ ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ ከፍተኛ ሃገራዊ ጥቅም ማስገኘት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ አገራችን በከፍተኛ ደረጃ የሰው ኃይል ወደ ውጭ ከሚፈልሱባቸው አገሮች አንዷ መሆኗ እሙን ነው፡፡ ይህ በሀገር ውስጥ ያለውን የሰለጠነ የሰው ሃይል ፍልሰት በተወሰነ ደረጃ መቀነስ ላይ ትኩረት ሰጥቶ የመስራትን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በውጭ ሃገር ከሚኖሩ የዳያስፖራ አባላት ጋር ጠንካራ ትስስር በመፍጠር በሃገር ውስጥ በሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ በንቃት የሚሳተፉበትንና ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ምቹ ሁኔታ የመፍጠር አስፈላጊነትን በጉልህ የሚያመለክት ነው፡፡

## 2. የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ፖሊሲ መነሻና አስፈላጊነት

የዳያስፖራ ፖሊሲያችን መነሻ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የውጭ ጉዳይና አገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ነው፡፡ በዚህ ሰነድ ውስጥ በውጭ  የሚኖሩ  ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በጥናትና ምርምር ሊያበረክቱ ከሚችሉትና በአገራቸው ልማት ኢንቨስት በማድረግ ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ በተጨማሪ በተለያዩ መንገዶች በጣም ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ በማስታዎስ መንግስት ይህንን ተገንዝቦ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ወዳጅ የሆኑ ግለሰቦች በዚሁ መስክ ሚናቸውን በአግባቡ እንዲጫወቱ ለማበረታታትና በተቻለ መጠን ለማስተባበር ጥረት ማድረግ እንዳለበት ይገለፃል፡፡ በዚህ መነሻ የዳያስፖራ አባላት በትውልድ አገራቸው እየተካሄዱ በሚገኙ የሰላም፣ የልማት፣ የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ሂደቶች ላይ በመሳተፍ ራሳቸውንና አገራቸውን መጥቀም እንዲችሉ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ስራውን የሚያስተባብር የዳያስፖራ ተሣትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በማቋቋም፣ የኢትዮጵያ

ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ አዋጅ በማዉጣት፣ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በአገር ውስጥ በሚገኙ ባንኮች በውጭ ምንዛሪና በብር ሂሳብ ከፍተው እንዲጠቀሙ ማድረግና በመሳሰሉት መንገዶች የተለያዩ አበረታች እርምጃዎችን በመንግስት በኩል ተወስዷል። ሆኖም ዳያስፖራው ከትውልድ አገሩ ጋር በጥብቅ እንዲተሳሰርና ያለውን ዕምቅ የፋይናንስ፣ ዕውቀት ና ሙያዊ አቅም በተሟላና በተቀናጀ መልኩ ሥራ ላይ እንዲያውል የሚያስችል በቂ እንቅስቃሴ ተደርጓል ለማለት አያስደፍርም፡፡

በመሆኑም የዳያስፖራውን አገራዊ ተሳትፎ ለመደገፍና ለማበረታታት እስከ አሁን የወጡ የህግ ማዕቀፎችን በተቀናጀ መንገድ በመፈጸም ዳያስፖራው በትውልድ ሀገሩ እየተመዘገበ ስላለው የሰላም፣ የልማትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በቅርበት ተገንዝቦ በተቀናጀ መልኩ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የበኩሉን ሀገራዊ ግዴታ እንዲወጣ ለማድረግ፣ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በሚኖሩባቸው ሃገራት መብትና ጥቅማቸው እንዲጠበቅላቸው ለመደገፍና በአገር ውስጥ የታዩ የዳያስፖራ ተሳትፎ ማነቆዎችን ለመፍታት ሃገራዊ የዳያስፖራ ፖሊሲ መቅረጽ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 3. የዳያስፖራ ፖሊሲ ትርጉምና ዓላማ

### 3.1. ትርጉም፡-

**የኢትዮጵያ ዳያስፖራ** ማለት ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ማለት ነው።

**የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ፖሊሲ** ማለት በአንድ በኩል በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ የሚሰጡትን አገልግሎቶች፤ በሌላ በኩል አገራችን በውጭ አገራት ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያንን የዕውቀት፣ የሙያ፣ የፋይናንስ፣ የግንኙነትና ሌሎች አስተዋፅኦዎችን ለመጠቀም እንዲያስችላት የሚረዱ ስፋት ያላቸው ግቦች፣ ስትራቴጂዎችና ተግባራት የተገለፀበት ሰነድ ነው፡፡

### 3.2 የዳያስፖራ ፖሊሲው አጠቃላይ ዓላማ

የፖሊሲው ዓላማ በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያዊ ከትውልድ ሀገሩ ጋር ያለውን ትስስር በማጠናከር በአገሩ ልማት፣ ሰላምና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ጠንካራ ተሳታፊ ሆኖ ራሱን ጠቅሞ ትውልድ አገሩንም በመጥቀም በጋራ ለማደግ የሚያስችል አመቺ ሁኔታ መፍጠርና በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን መብትና ጥቅም ማስከበር ነው።

## ክፍል ሁለት

## 4. የፖሊሲው መሰረታዊ መርሆዎች

በዳያስፖራው ዘርፍ ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸዉ ዓበይት ጉዳዮች በፖሊሲው ተለይተዋል፡፡ በእነዚህ ላይ ብቃት ያለው ስራ በመስራት የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት ከትውልድ አገራቸው ጋር ያላቸውን አጋርነት ማጎልበት እንደሚቻል ታምኖበታል። ይህ አጋርነት ሁሉም ወገኖች በሚጋሩት አገራዊ ጥቅም ላይ የሚመሰረትና በአገሪቱ የፖሊሲ አቅጣጫዎች የሚመራ በመሆኑ በብሄራዊ ጥቅም ዙሪያ መታየት ባለባቸው መርሆዎች ይመሰረታል። እነዚህም ፡-

**4.1 ሴክተር አቀፋዊነት (A Sector Wide Approach)**

የዳያስፖራ ጉዳይ በአንድ ሴክተር ብቻ ያልታጠረ ከብዙ ሴክተሮች ጋር ተያያዥነት ያለው በመሆኑ ፖሊሲውን ለማሳካት የሚከናወኑ ተግባራት ከሌሎች ተጓዳኝ ሴክተሮች እንቅስቃሴ ጋር ተጣጥመው መከናወን ይኖርባቸዋል፣

**4.2 ውጤታማነት (Effectiveness)**

የጥረታችን ሁሉ የመጨረሻ ግብ ድህነትን ማስወገድ እንደመሆኑ መጠን ይህ የዳያስፖራ ፖሊሲ ድህነትን ለማስወገድ የሚደረገውን ትግል ለማሳካት ወይም በውጤት ለማጠናቀቅ በሚያስችል መልኩ ተፈጻሚ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠይቃል፣

**4.3 የሃብት አጠቃቀም (Resources Utilization)**

የዳያስፖራ ፖሊሲውን ለማስፈጸም የምንከተላቸው ስትራተጂዎች በሙሉ ካለን ውስን ሃብትና ንብረት አቅም ጋር ተገናዝቦ መታየት ይኖርበታል። ስለሆነም የፖሊሲው ተፈጻሚነት እንደሃገሪቱ የእድገት ደረጃ እየታየ የሃብትና ንብረት አጠቃቀም ሥርዓት ጋር ተጣጥሞ የሚከናወን ይሆናል፣

**4.4 ተደጋጋፊነት (Complementarity)**

የዳያስፖራ ፖሊሲው ከሌሎች ብሔራዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች የምዕተ ዓመት የልማት ግቦች አንዱ ከሌላው ጋር ተደጋግፎ እንደሚሄድ ታሳቢ ይደረጋል፣

**4.5 አሳታፊነት (Participatory)**

የዳያስፖራ ፖሊሲው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን፣ የዳያስፖራውን ህጋዊ እንዲሁም የሴቶችን ተሳትፎ በሚያረጋግጥ መንገድ የሚፈጸም ይሆናል፣

**4.6 ግልጽነት (Transparency)**

የዳያስፖራን ፖሊሲ በማስፈጸም ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት ግልጽነት ያለውን አሰራር የሚከተሉ ይሆናል፣

**4.7 አጋርነት (Partnership)**

የዳያስፖራውን ሁለንተናዊ አገራዊ ተሣትፎ ለማጎልበትና በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ ፖሊሲው በአገር ውስጥ ከሚገኙ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላትና ዳያስፖራው ከሚኖርባቸው አገራት ጋር በአጋርነት የሚፈፀም ይሆናል፣

# 5. የፖሊሲው ዋና ዋና ግቦች

## 5.1 በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንን መብትና ጥቅም ማስጠበቅ፡-

5.1.1 በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የምዝገባ ስርዓት ይዘረጋል፣

5.1.2 በኤምባሲዎች፣ ቆንስላ ጽ/ቤቶችና ንግድ ጽ/ቤቶች የሚሰጡ አገልግሎቶችን በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በሚገባ እንዲያውቋቸው ለማድረግ የሚያስችሉ ወቅታዊ አገራዊ መረጃዎችንና ፖሊሲዎችን የማስተዋወቅ ስራዎች ይካሄዳሉ፣

5.1.3 በውጭ አገር የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸው ኢትዮጵያዊያን በአደጋ ጊዜ ማንነታቸዉን በመለየት ድጋፍ ለመስጠት በሚስዮኖቻችን በኩል የቆንስላ መታወቂያ ካርድ እንዲሰጥ ይደረጋል፣

5.1.4 ኢትዮጵያዊያን በሚኖሩባቸው አገሮች በሚከሰቱ ድንገተኛ አደጋዎችና አለመረጋጋቶች ሳቢያ ከሚፈጠሩ ችግሮች ለመታደግ የሚደረጉ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፣

5.1.5 ሠራተኛንና አሰሪን የሚያገናኙ ኤጀንሲዎች ከሚሲዮኖች ጋር ግንኙነት ኖሯቸው የላኳቸውንና የተቀበሏቸዉን ሰራተኞች በሚመለከት በሚሲዮኖች በኩል ጥብቅ ክትትል ይደረጋል፣ ወጥ የሆነ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት እንዲኖርና ለዉጤታማነቱ በሚሲዮኖችና በአገር ውስጥ ጉዳዩ ከማመለከታቸዉ መስሪያ ቤቶች መካከል በኔትወርክ ግንኙነት ይፈጠራል፣

5.1.6 ኢትዮጵያዊያን በብዛት ለስራ ከተሰማሩባቸው አገሮች ጋር የሥራ ስምምነት ለመፈራረም እየተደረገ ያለው ጥረት ይጠናከራል፣

## 5.2. የኢንቨስትመንት፣ የንግድና ቱሪዝም ተሳትፎን ማጐልበት

### 5.2.1. ኢንቨስትመንት፡-

5.2.1.1 ውጭ የሚገኙ ሚሲዮኖቻችን ወቅታዊ የኢንቨስትመንት መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር በዳያስፖራው ላይ ያተኮረ ፕሮሞሽን እንዲያካሂዱ ይደረጋል፣

5.2.1.2 ማንኛውም በውጭ የሚኖር የዳያስፖራ አባል አግባብነት ባላቸው የኢንቨስትመንት መስኮች መዋዕለ ንዋዩን በግል ወይም ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገራት ባለሀብቶች ጋር በሽርክና ኢንቨስት እንያደርግ ይበረታታል፣

5.2.1.3 የፌዴራልና የክልል ኢንቨስትመንት ጽ/ቤቶችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ዳያስፖራው በኢንቨስትመንት መስክ ለመሰማራት የሚያደርጋቸውን ጥረቶችና የሚያቀርባቸውን ፕሮጀክቶች በግንባር ቀደምትነት እንዲያበረታቱና እንዲተባበሩ ይደረጋል፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ይሰጣል፣

5.2.1.4 በአገሪቱ የኢንቨስትመንት ደንብና መመሪያ መሰረት የመሬት አቅርቦትን ቀልጣፋ ለማድረግ በሚዘጋጁ የኢንዱስትሪ ዞኖች እና የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ፓርኮች ውስጥ ዳያስፖራው በመሣተፍ ኢንቨስት እንዲያደርግ ይበረታታል፣

5.2.1.5 ኢትዮጵያዊያን ዳያስፖራዎች በትውልድ አገራቸው በኢንቨስትመንት መስክ ለመሳተፍ ከሚኖሩባቸው ሀገሮች ብድር ወይም የብድር ዋስትና ዕድል ሲያገኙ መንግሥት በአገሪቱ የብድር ፖሊሲ መርሆዎች ላይ ተመስርቶ አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት ድጋፍ ያደርግላቸዋል፣

5.2.1.6 የዳያስፖራ አባላት የቅድሚያ ትኩረት በሚሰጧቸው የኢንቨስትመንት መስኮች በግል ወይም በጋራ ኢንቨስት እንዲያደርጉ መንግስት የፕሮጀክቶች ፕሮፋይል በመቅረፅ ወደ ስራ የሚገቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

5.2.1.7 በውጭ አገራት የሚኖሩ የዳያስፖራ አባላት በትውልድ አገራቸው ውስጥ ለሚሰሩት ስራ የሚያቋቁሙትን የንግድ አክሲዮን በየአካባቢያቸዉ በሚገኙ ሚሲዮኖች አማካኝነት ሕጋዊ በማድረግ በአገር ውስጥ ለማስመዝገብ የሚቻልበት አሠራር ይደረጋል፣

**5.2.2. ንግድና ቱሪዝም፡-**

5.2.2.1 የዳያስፖራ አባላት ንግድን በሚያስፋፉ መንግስታዊ ተቋማት ውስጥ በክህሎታቸው እንዲሳተፉና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይበረታታሉ፣

5.2.2.2 ዳያስፖራው በአገር ውስጥ ለሚገኙ አስመጪና ላኪዎች እንዲሁም አስጎብኚ ድርጅቶች በገበያ ኢንተለጀንስ ዘርፍ፣ በአገናኝነትና በሽያጭ ሠራተኛነት የዳበረ ልምዱን በማካፈል ራሱንና ድርጅቶቹን ተጠቃሚ እንዲያደርግ ይበረታታል፣

5.2.2.3 ዳያስፖራው ለሀገራችን ዋና ዋና ምርቶች ሰፊ ገበያ በማፈላለግና የንግድ ሸሪክ በመሆን ራሱንና ላኪዎችን ተጠቃሚ እንዲያደርግ ሁኔታዎች እንዲመቻቹለት ይደረጋል፣

5.2.2.4 ከአገራችን ምርቶች በተለይም ባህላዊ የዕደ ጥበብ ውጤቶች መካከል የማህበረሰቡ አባላት በብዛት በሚኖሩባቸው አገሮች ገበያ ሊያገኙ የሚችሉትን በመለየት ምርቶቹን ለሚያመርቱና ለሚያከፋፍሉ ልዩ የፕሮሞሽን ፓኬጅ ይዘጋጃል፣

5.2.2.5 የዳያስፖራ አባላትና ለአጭር ጊዜ የትምህርትና የስልጠና ቆይታ ወደ ውጭ የሚሄዱ ኢትዮጵያዊያን ቱሪዝምን በማስፋፋት ሥራ ላይ እንዲሳተፉ ይበረታታሉ፣

5.2.2.6 ኢትዮጵያዊያን ህጻናትን በጉዲፈቻ ወስደው የሚያሳድጉ ቤተሰቦችና ታዳጊ ህፃናት የኢትዮጵያ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ መስህቦችና ቦታዎችን እንዲጎበኙና የቱሪዝም ሀብቶቻችንን እንዲያስተዋውቁ የጉብኝት ፓኬጅ ይዘጋጃል፣

## 5.3. የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ፡-

**5.3.1** የዳያስፖራው አባላት አግባብነት ባላቸው የመንግስት መ/ቤቶችና ተቋማት ወዘተ ውስጥ በሙያቸውና በልምዳቸው በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት ለማገልገል ከጠየቁ ባለው የመንግሥት መመሪያ መሠረት የሥራ ዕድል እንዲመቻችላቸው ይደረጋል፣

**5.3.2** ከፍተኛ የትምህርት ዝግጅትና ልምድ ያካበቱ ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት በሀገር ውስጥ በከፍተኛ ትምህርትና በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ውስጥ የሚያስተምሩበትና የሚመራመሩበት መንገድ ይመቻቻል፣

**5.3.3** በዕዉቀታቸዉና በልምዳቸው አገራቸውን ለማገልገል ለሚመጡ ከፍተኛ ባለሙያዎች የአገሪቱ አቅም በፈቀደው መሠረት ማበረታቻ ይደረግላቸዋል፣

**5.3.4** መንግስት ትኩረት በሚሰጣቸው የምርምር መስኮች ውስጥ ልዩ ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎች ጥናቶችን እንዲያካሂዱና እንዲያማክሩ ይበረታታሉ፣

**5.3.5** ወደ አገራቸው ገብተው ልዩ ክህሎት በሚጠይቁ (የትምህርት፣ የጤና፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ወዘተ) መስኮች በመስራት ላይ ያሉ የዳያስፖራ አባላትን በተጠናከረ መልኩ ለመጠቀም የሚያስችል ሁኔታ ይመቻቻል፣

**5.3.6** በውጭ ሀገር በሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚማሩ ወጣት ዳያስፖራዎች በአገር ውስጥ በሚገኙ የመንግስትና የግል ተቋማት ውስጥ የሥራ ልምምድ የሚያደርጉበት ፕሮግራም ይመቻቻል፣

**5.3.7** ወደ አገር ቤት መጥተው ዕዉቀታቸዉንና ክህሎታቸዉን ለማስተላለፍ ፍላጎት ያላቸዉን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪዎች ያበረታታል፣

**5.3.8** በመካከለኛው ምሥራቅና በጎረቤት ሀገሮች የሚኖሩ ዳያስፖራዎች ከፍተኛ ትምህርታቸውን በተልዕኮ እንዲማሩ ይበረታታል፣ የሚማሩበት ሥርዓት ይዘረጋል፣ በውጭ አገራት የሚገኙና በኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት የተቋቋሙ የኮሚኒቲ ት/ቤቶችም የሚስፋፉበትና የሚጠናከሩበት አሰራር ይዘረጋል፣

**5.3.9** በዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዘርፍ ከዳያስፖራው በዕርዳታ የተገኙ ቁሳቁሶች በአፋጣኝ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡበትና ጥቅም ላይ የሚውሉበት መንገድ ይመቻቻል፣

## 5.4. የውጭ ምንዛሪ ማስገቢያ መንገዶችንና ተሣትፎን ማሳደግ

**5.4.1.** ወደ አገር ቤት ጠቅልለው የሚመለሱ ኢትዮጵያዊያን ዳያስፖራዎች በውጭ ያፈሩትን የውጭ ምንዛሪና በአገልግሎት ያገኙትን የጡረታ አበል ገቢያቸውን ወደ አገር ቤት ይዘው እንዲመጡ የሚያበረታታ አሰራር ይዘረጋል፣

5.4.2. በውጭ የሚኖሩ የዳያስፖራ አባላት ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች (ለቤተሰብ፣ ለኢንቨስትመንት ወዘተ) ወደ ሀገር የሚልኩት የውጭ ምንዛሪ ገንዘብ በህጋዊ መንገድ እንዲሆን የሚያበረታታ አሰራር ይዘረጋል፣

5.4.3. ሚሲዮኖቻችን ከሀገር ውስጥ የኢትዮጵያ ባንኮች ጋር በመተባበር በየተወከሉባቸዉ አገሮች በመደበኛ መንገድ ገንዘብ ወደ አገር ቤት የማስተላለፍ አገልግሎት ከሚሰጡ ባንኮች/ድርጅቶች ጋር በመደራደር ዳያስፖራው የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲያገኝ ጥረት ይደረጋል፣

5.4.4. ዳያስፖራው በትውልድ አገሩ ለሚካሄደዉ ኢንቨስትመንቶችና የልማት ተግባራት ከአገር ውስጥ ባንኮች ለወሰዱት የብር ብድር እንዲሁም ለሚገዟቸው የፌደራልና የክልል ቦንዶች በውጭ ምንዛሪ የሚከፍሉበት አሰራር ይቀየሳል፣

## 5.5. ባህላዊ እሴቶችን ማዳበርና ገፅታ ግንባታን ማትጋት

5.5.1. በርካታ የኮሚኒቲ ማህበራት ባሉባቸው አገሮች የባህል ማዕከላትን በመክፈት ዳያስፖራው ከሀገሩ ባህል፣ ታሪክና ቋንቋ ጋር እንዲተሳሰር ይደረጋል፣

5.5.2. የዳያስፖራ አባላት በትውልድ አካባቢያቸው የባህል ማዕከላትና ሙዚየሞችን በመገንባት ታሪካቸውንና ባህላቸውን እንዲጠብቁ ይበረታታሉ፣ አስፈላጊው ድጋፍም ይሰጣል፣

5.5.3. የዳያስፖራ አባላት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ለሚያዘጋጁቸው የባህልና የኪነት ትርዒቶች እንዲሁም የስፖርት በዓላት አስፈላጊው ማበረታቻና ድጋፍ ይሰጣቸዋል፣

5.5.4. ወጣቶችን እንዲሁም ከኢትዮጵያ በጉዲፈቻ የሄዱትን ዳያስፖራዎች ከትውልድ ሀገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስር ለማጠናከር የተደራጀ የአገርህን ዕወቅ የጉብኝት፣ የቋንቋዎች ትምህርት እና የባህል ትውውቅ ፕሮግራሞች ይቀረፃሉ፡፡

## 5.6. በዴሞክራሲያዊ ሂደት የሚኖረውን ተሳትፎ ማሳደግ

5.6.1. የምርጫ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት በውጭ የሚገኙ የኢትዮጵያ ዜጎች በምርጫ እንዲካፈሉ የምርጫ ቦርድ ከኢትዮጵያ ዳያስፖራ ጋር በመተባበር የሎጂስቲክስ ስርዓት የሚዘረጋበትን መንገድ ያጠናል፣

5.6.2. የሌላ አገር ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸውና ኑሯቸው በወሳኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ የሆኑትን ዜጎች የምርጫ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በሚኖሩበት አካባቢ በምርጫ ለማሳተፍ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፣

5.6.3. በአገር ውስጥ በሚከናወኑ የፖሊሲ ጥናቶችና ቀረፃዎች የዳያስፖራ አባላት እንዲሳተፉ ሁኔታዎች ይመቻቻል፣

## 5.7. የግብረ ሰናይና የልማት ማህበራትን ማትጋት

**5.7.1.** በዳያስፖራ የሚደረግ የግብረ ሰናይ መዋጮ ከማንኛውም ሀይማኖታዊና የፓለቲካ ግንኙነቶች የተላቀቀ መሆኑን በማረጋገጥና ሥርአት ባለው መንገድ እንዲገባ በማድረግ ይስተናገዳል፣

**5.7.2.** የተደራጁ በጎ ፈቃደኞችን አስተዋጽኦ በማትጋት ተደራጅተው የነፃ አገልግሎት የሚሰጡበት አሰራር ይዘረጋል፣

**5.7.3.** ዳያስፖራው በአገሩ ለሚያከናውናቸው የግብረ-ሰናይ ስራዎች እንዲውሉ ለሚያስመጣቸው ቁሳቁሶች አቅምን ያገናዘበና ተመጣጣኝ የሆነ ማበረታቻ የሚደረግበት አሰራራር ይዘረጋል፣

**5.7.4.** በውጭ አገራት የተቋቋሙ የልማት ማህበራት በአገር ቤት ከእናት የልማት ማህበራት ጋር የሚገናኙበትና ትስስራቸው የሚጠናከርበት መንገድ ይመቻቻል፤ ከውጭ የሚደረገውን የልማት መዋጮ ማሳደግ የሚያስችልና ገንዘቡን አግባብ ባለው መንገድ በፍጥነት ወደ ልማት ማስገባት የሚያስችል አሰራር ይጎለብታል፣

## 5.8. የኢትዮጵያን ገጽታ በሚገነቡ ጉዳዮች ላይ ማሳተፍ

**5.8.1.** የኢትዮጵያን ምርቶች፣ ባህል፣ ታሪክ፣ በአገራችን እየተካሄዱ የሚገኙ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጦችን በሚያስተዋዉቁ በውጭ አገራት በሚዘጋጁ መድረኮች እንዲሳተፉ ይደረጋል፣

**5.8.2.** ወቅታዊ አገራዊ ሁኔታዎችን እንዲከታተሉ በማድረግ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅምና ገጽታ በሚገነቡ ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ ይደረጋል፣

## ክፍል ሦስት

# 6 የፖሊሲው ስትራቴጂዎች

## 6.1 አስተማማኝ የመረጃ አያያዝና ሥርጭት ሥርዓት መዘርጋት

### 6.1.1 የመረጃ አገልግሎትን ማስፋት

**6.1.1.1** በዳያስፖራ ላይ ያተኮረ የመረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና ስርጭትን ተግባራዊ ለማድረግ የተጠናከረ የዳያስፖራ መረጃ ቋትና ድረ-ገጽ እንዲደራጅ ይደረጋል፣

**6.1.1.2** መረጃዎች በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ (ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ዌብሳይት፣ ኢ-ሜይል ወዘተ) በህትመት ውጤቶች አማካይነት ለዳያስፖራው የሚደርሱበት ስርዓት ይዘረጋል፣

**6.1.1.3** በሀገር ውስጥና በርካታ የዳያስፖራ አባላት በሚገኙባቸው ሀገራት የስብሰባ መድረኮችን፣ ሲምፖዚየሞችን፣ ኤግዚቢሽኖችንና የፊልም ፌስቲቫሎችን በማዘጋጀት ዳያስፖራውን ለማገናኘትና ለማወያየት ትኩረት ይደረጋል፣

**6.1.1.4** ዳያስፖራው በሀገር ውስጥ ስለሚካሄዱ የሰላም፣ የልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደቶች የተሟላ ግንዛቤ እንዲጨብጥ ለማድረግ የውጭ የኮሚዩኒቲ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች እንዲስፋፉ ይበረታታል፣

### 6.1.2 ቋሚ የመረጃ ልውውጥ መድረኮችን መፍጠር

#### 6.1.2.1 በአገር ቤት ቋሚ የዳያስፖራ ቀን በዓል አከባበር

6.1.2.1.1 አገር አቀፍ ደረጃ የሚከበር የዳያስፖራ ቀን ይኖራል፣ በተጨማሪም በርካታ የዳያስፖራ አባላት በሚመጡባቸዉ ዓመታዊ የበዓላት መድረኮች ይዘጋጃሉ፣

6.1.2.1.2 በክልል አቀፍ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ክልሎችም ተወላጆቻቸውን የሚያሳትፉበት ተጓዳኝ መድረኮች፣ ከዳያስፖራው ጋር ተያያዥነት ያለው ተግባር የሚያከናዉኑና አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ፣ ቢዝነሶችና ሙያተኞች በአገር ውስጥ ከሚገኙ አቻዎቻቸውና ተቋማት ጋር ግንኙነት እና ትስስር የሚፈጥሩበት ሁኔታ ይመቻቻል፣

#### 6.1.2.2 በውጭ ከዳያስፖራ ጋር የሚካሄዱ የግንኙነት መድረኮች

6.1.2.2.1 መንግስት ከዳያስፖራው ጋር በውጭ የሚያካሂዳቸው መድረኮች በታቀደና ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ይሆናሉ፣

6.1.2.2.2 በተለያዩ ክፍለዓለማት የሚኖሩ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት ማህበራዊ ግንኙነታቸውን የሚያጠናክሩባቸው ዓመታዊ ፌስቲቫሎች እንዲያዘጋጁ አስፈላጊ ድጋፍ ይሰጣል፣

## 6.2 ለዳያስፖራው ተሳትፎ ዕውቅና መስጠት

**6.2.1** ለትውልድ አገራቸው ሰላም፣ ልማትና ዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ግለሰቦችና ማህበራት በፌዴራል እና በክልል መንግስታት ዕውቅና የሚሰጥ የሽልማት ስርዓት ይዘረጋል፣

## 6.3 የተደራጀ ተሳትፎን ማትጋት

### 6.3.1 ያሉትን ማህበራት ማጠናከር አዳዲስ እንዲፈጠሩ ማገዝ

6.3.1.1 ልዩ ልዩ የዳያስፖራ ማህበራት የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የሙያ፣ የልማት፣ የማህበረሰብ ወዘተ እንዲቋቋሙ ይበረታታሉ፣ የተቋቋሙትም የሚጠናከሩበት ስልት ይቀየሳል፣

6.3.1.2 የብሄራዊ የጋራ ይሁንታ መሰረተ-ሃሳብን በሚገባ በማስተዋወቅ የኢትዮጵያ ዳያስፖራዎች በያሉበት የመሰረቷቸው ማህበራት መረጃዎች በአግባቡ ይያዛሉ፣ ሌሎች አዳዲስ ማህበራት እንዲመሰረቱ ይበረታታሉ፣ በተደራጀ መልኩ አገራቸውን እንዲደግፉ ለማድረግ የሚፈልጉትን ድጋፍና ሊያበረክቱ የሚፈልጉትን አስተዋፅኦ በአግባቡ በመለየት ድጋፍ ይሰጣል፣

6.3.1.3 የኮሚኒቲ ማህበራት ከፋውንዴሽኖች፣ ከሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ ከኢትዮጵያ ሚሲዮኖችና ከግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጋር ተቀናጅተው መስራት የሚችሉበትን ሁኔታ ያበረታታል፣

6.3.1.4 የዳያስፖራ የሙያተኞች፣ የተማሪዎች፣ የሴቶች ወዘተ ማህበራት በመረጃ መረብ እንዲገናኙ እርስ በእሳቸዉ እንዲተዋወቁና ልምድ እንዲለዋወጡ፣ ዓለም አቀፋዊ የዳያስፖራ ማህበራት መረብ በመመስረት በአገር ቤት ካሉ ተመሳሳይ ማህበራት ጋር እንዲተዋወቁ የሚያስችሉ ስራዎች ይከናወናሉ፣

6.3.1.5 ተመላሾች በአገር ቤት ተደራጅተው ተሳትፎዋቸውን እንዲያጠናክሩና አዳዲስ ተመላሾችን በተለያዩ ዘርፎች እንዲያግዙ ድጋፍ ይሰጣል፣

### 6.3.2 ለወጣት ዳያስፖራዎች የተደራጀ ተሳትፎ ልዩ ትኩረት ይሰጣል

6.3.2.1 በውጭ በተለያየ መልክ ተደራጅተው የሚገኙ ወጣቶችን መረጃ በመያዝ በአካልና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ አማካኝነት የተጠናከረ ግንኙነት ይመሰረታል፣ አዳዲስ የወጣትና የተማሪዎች ማህበራት እንዲደራጁ ድጋፍ ይደረጋል፣ የዓለም አቀፍ ማህበራት በድረ-ገጽ መረብ እንዲጠናከሩ ያተጋል፣

6.3.2.2 በውጭ አገር ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስብስቦች ጋር በመተባበር በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ያሉ ወጣቶች ሀሳባቸውን የሚለዋወጡበት ወጣቶችን ማዕከል ያደረገ የኢትዮጵያዊያን የባህል፣ የስነ ፅሁፍ፣

የኪነ-ጥበብና የስፖርት ዝግጅቶች በየዓመቱ እንዲዘጋጁ ይበረታታል፣ የዕውቀትና ቴክኖሎጂ ልምድ ልውውጥ አሰራር ይዘረጋል፣ ወጣቱ ተደራጅቶ ዋና ተዋናይ የሚሆንበት ሁኔታ ይመቻቻል፣

6.3.2.3 በውጭ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች በሚገኙባቸዉ የመንግስትና የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋመት በመገኘት በአገር ቤት ያሉት ዕድሎች በስፋት ይተዋወቃሉ፣ በስራ ላይ የሚገኙ ሌሎች ወጣት ፕሮፌሽናሎችን በተመለከተም ተመሳሳይ ሴሚናሮች የሚካሄዱበት ሁኔታ ይመቻቻል፣

6.3.2.4 የአገራችንን የልማት ስትራቴጂ እንዲሁም ባህልና ታሪክ እንዲያውቁ ለወጣት የዳያስፖራ አባላት ሴሚናሮች፣ ሲምፖዚየሞች ወዘተ እንዲዘጋጁ ይደረጋል፣

6.3.2.5 ከአፍሪካ ህብረት ፕሮግራም ጋር በማጣጣም ከአፍሪካ ወጣቶች የዳያስፖራ እንቅስቃሴ ጋር እንዲቆራኙ ጥረት ይደረጋል፣

**6.3.3** ወጣት ዳያስፖራዎች የበጐ ፈቃድ አገልግሎትን ለመደገፍ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፣

## 6.4 የትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ መስጠት

**6.4.1** የትውልደ ኢትዮጵያዊያን መታወቂያ ካርድ ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ከትውልደ አገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስርና ተሳትፎ የሚያሰፋና የሚያሳድግ ዋነኛና ቋሚ መሳሪያ ለማድረግ በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ የሚሰራ ይሆናል፣

## 6.5 የዳያስፖራ አባላትን መደገፍ

**6.5.1** ጠቅልለው ወደ ትውልድ አገራቸው የሚመለሱ የዳያስፖራ አባላት ይዘው የሚገቡት የግል መገልገያ በመንግስት መመሪያ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፣

**6.5.2** የዳያስፖራ አባላት በግልና በማህበር ተደራጅተው በክልሎች፣ አዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች በቁጠባ ሥርዓት መሰረት የመኖሪያ ቤት የሚያገኙበት መንገድ በጥናት ላይ የተመሰረተ አሰራር ይዘረጋለታል፣

**6.5.3** የኢትዮጵያ ሚስዮኖች በሌሉባቸዉ በርካታ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በሚኖሩባቸው አገሮች የክብር ቆንስላ የሚሾምበት ወይም ከኮሚኒቲ ማህበራት ጋር በመተባበር ዜጐች አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያሰፋል፣ የተንቀሳቃሽ የአገልግሎት አሰራርን ያበረታታል፣

**6.5.4** በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በኮሚኒቲዎች በኩል የሚያደርጉትን ዕገዛ በማጠናከር የኮሚኒቲ ማህበራት እንዲስፋፉና የሥራተኛ አያያዝ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች የእርስ በርስ መደጋገፍ እንዲጠናከር ያተጋል፡፡ ከኮሚኒቲው ጋር በመተባበር ለአጭር ጊዜ የሚቆዩበት መጠለያ ማቋቋምን በሚመለከት በጥናት ይመልሳል፣

**6.5.5** ወደ አገራቸው የሚመለሱ የዳያስፖራ አባላት በአገሪቱ ህግ መሠረት የስራ ዕድል እንዲያገኙ አሠራር ይዘረጋል፣

**6.5.6** ጉዲፈቻ ሕጻናት መልካም ስብዕናን ተላብሰው የሚያድጉበትና መብትና ጥቅማቸው የሚጠበቅበት እንዲሁም ከትውልድ ሀገራቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ተጠብቆ የሚቆይበት አሰራር ይዘረጋል፣

**6.5.7** መንግስት ዳያስፖራን አስመልክቶ በሚኖሩ አካባቢያዊ፣ አህጉራዊና ዓለም ዓቀፋዊ መድረኮች ተሳትፎውን አጠናክሮ ይቀጥላል፣

# 7 የፖሊሲው አስፈፃሚ አካላት

**7.1** የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳያስፖራ ፖሊሲውን አፈጻጸም በበላይነት ይመራል፣

**7.2** የተለያዩ የፌዴራልና የክልል መንግስት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችና ባለድርሻ አካላት የሚወከሉበት የዳያስፖራ ብሔራዊ ካውንስል ይቋቋማል፣

**7.3** በአገር ቤት በተለያዩ መስኮች ከሚሳተፉ ተመላሽ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት የተውጣጣ አማካሪ ካውንስል ይቋቋማል፤ ተመሳሳይ አማካሪ ካውንስል በሚሲዮኖች ዙሪያም ይቋቋማል፣

**7.4** የክልል የዳያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች የየክልሎቻቸዉን የዳያስፖራ ተሳትፎ ይመራሉ፣

**7.5** የዳያስፖራ ተሳትፎ ማጐልበቻ ስራዎችን በቅንጅት መምራት እንዲቻል በውጭ ጉዳይ የሚመራ የክልሎችና የፌዴራል መስሪያ ቤቶች የዳያስፖራ ማስተባበሪያዎች ጽ/ቤቶች የጋራ መድረክ ይዋቀራል፣ ቀጣይነት፣ ተጠያቂነትና ተገቢው አቅም እንዲኖራቸዉ ይደረጋል፣

**7.6** በአገር ውስጥና በውጭ አገራት የሚገኙ የዳያስፖራ አደረጃጀቶች እርስ በእርሳቸውና ከሚመለከታቸው ጋር ቋሚ ግንኙነት የሚመሠርቱበት አሠራር ይዘረጋል፣

**7.7** የፖለሲው አስፈፃሚ አካላትን አሠራር በጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረተ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡